በዘወትር የአባታችን ሆይ ጸሎታችን ላይ አባቶቻችን ለድንግል ማርያም ሰላምታ እንድናደርስ ሥርዓት ሠርተዋል። አባታችን ሆይ ከወንጌል የተገኘ ጸሎት እንደ ሆነ ሁሉ 'እመቤታችን ሆይ' የሚለው ሰላምታም ከእዚያው ከወንጌል ቃል በቃል የተገኘ ጸሎት ነው። ክርስቶስም 'አባታችን ሆይ በሉ' አለ እንጂ 'ከአባታችን ሆይ በስተቀር ሌላ ነገር እንዳትሉ' አላለም። እንደ ዳዊት ያሉ ነቢያት የእግዚአብሔር ከተማ ለነበረችው ለኢየሩሳሌም እንደዘመሩ እኛም የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን ለተመረጠችው ድንግል እንዘምራለን። ኤልሳቤጥ እናትና ልጅን አከታትላ 'አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው' ብላ አብራ እንዳመሰገነች እኛም ድንግሊቱን ከማሕፀንዋ ፍሬ ጋር አብረን እናመሰግናታለን።

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ 'ግነዩ፡ለእግዚአብሔር፡ወጸውዑ፡ስሞ፡እንዘ፡ኢትፈሪጡ፡እሞ' 'ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ስሙንም ጥሩ ፤ እናቱን ሳታሰቀሩ' እንዳለ ድንግሊቱን ከፍሬዋ ጋር ፣ ዙፋንዋን ከንጉሡ ጋር አብረን እንጠራለን።[253] ከሙሴ ጋር 'ሕዝቡም በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ' ተብሎ እንዲነገርለት የፈቀደ አምላክ 'በአሚነ፡ዚኣሁ፡ለማርያም፡ጎባኒ' 'እርሱን በማመን ለማርያም አንገዛ' ስንል

253 መልክዓ ጥርባን ፣ ድጓረ ዕርገት ፣ መልክዓ ጉባኤ ፪፻፳፱ ፣ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

አይቃወመንም፡፡ ዘጸ. ፲፬፥፴፮ ከዳዊት ጋር ‘ስለ እኔም ፣ ስለ ባሪያዬም ስለዳዊት ይህችን ከተማ አድናታለሁ’ ብሎ ራሱን ከባሪያው ጋር የጠራ አምላክ ‘አግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ፣ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ’ ብለን ከእናቱ ጋር ስንጠራውስ አይሰማን ይመስላችኋል? ለነገሩ እንኳን ስለ ማርያም ‘በእንተ ጸላኢ’ ‘ስለ ጠላት’ ዲያብሎስ ብለህ እርሱን ታሳፍረው ዘንድ ማረን ብንለውም ይሰማናል፡፡ ፪ነገሥ. ፲፱፥፴፬ ይህን በኤልሳቤጥ ላይ ያደረ መንፈስ ቅዱስ ‘አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው’ አሰኝቶ አስተምሮናል፡፡

ለእመቤታችን ሰላምታ ለማቅረብ አባቶቻችን ‘ምን እንበላት?’ ብለው አልተጨነቁም፡፡ ምንም ዓይነት ቅኔ ብናዋጣ ለእመቤታችን ከእግዚአብሔር ከተላከላት ከገብርኤል ሰላምታ በላይ የተሻለ ሰላምታ ልናቀርብላት አንችልም፡፡ ስለዚህ ኤልሳቤጥ እንደተዋሰችው ተውሰን ‘በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን’ እያልን እናመሰግናታለን፡፡ ድንግል ሆይ የእኛን ምስጋና ለአንቺ ይሆናል ብለን አስቀድመን አናቀርብልሽም ፤ ብርሃናዊው መልአክ ከራማ ድረስ ወርዶ ባቀረበልሽ ሰላምታ ፣ እግዚአብሔር ልኮት በነገረሽ ውብ ምስጋና ግን ምስጋናሽን እንጀምራለን፡፡ ‘ገብርኤል ‘ደስ ይበልሽ የተባረክሽ ነሽ’ ሰላላት እኔ ደስ ይበልሽ አልላትም’ የሚል ሰው ካለ በዚህ አቋሙ

መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ያመሰገኑትን አምላክ 'ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ' ብሎስ እንዴት ሊያመሰግነው ይችላል?

ኤልሳቤጥ ክርስቶስን 'የድንግል ማርያም ፍሬ' ብላ ጠራችው። በእርግጥም ያለ ወንድ ዘር በመንፈስ ቅዱስ ግብር የፀነሰችው ልጅዋ ስለሆነ ክርስቶስ የድንግል ማርያም የማሕፀንዋ ፍሬ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ 'እግዚአብሔር ከሴት የተወለደ ልጁን ላከ' እንዳለ ክርስቶስ ከወንድ ያልተገኘ ከሴት ብቻ የተወለደ ነውና ለድንግሊቱ 'የማሕፀንሽ ፍሬ' መባል ይገባታል።[254] ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ክርስቶስ 'ከወንድና ከሴት ሩካቤ ቢወለድ ኖሮ ብዙ ሰዎች አምላክነቱን በካዱና ሐሰት ነው ባሉ ነበር። ስለዚህ እነሆ ከብቻዋ ከድንግል ተወለደ' ብሏል፡ ፡ 'ወይእዜሰ፡ናሁ፡ተወሊደ፡እምባሕቲታ፡ድንግል፡ማርያም' እንዲል።